| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ዐምዳዊ ፡ ጽሑፍ ፤ "ሐተታ ፡ መጻሕፍት" |
| ርእስ ፤ | "ሕይወቴ ።"<br>ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፤ |
| ደራሲ ፤ | ዐቃች ፥ ወሌ ፡ ነጋ ። |
| ዕለት ፤ | የካቲት ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጻም ። |
| መጽሔት ፤ | "ሥልጡንሕዝብና" ፥ ቍ.2018-003 ። |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ሐተታ ፡ መጻሕፍት ።

Books Review | revue de livres | مراجعة الكتب

"ሕይወቴ" ፡ የተሠኘው ፡
የደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡
ግል-ታሪክ ፡ መጽሐፍ ፡ ሐተታ ።

## « ሰው ፡ ቢታጣ ፥ ምድር ፡ ትመሰክር ፡ አፍ ፡ አውጥታ ። »

ወሌ ፡ ነጋ ።

"ሕይወቴ" ፡ በሚል ፡ ርእስ ፡ የደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ ግል-ታሪክ ፡ በመጽሐፍ ፡ ታተሞ ፡ ለገበያ ፡ በበቃ ፡ ሰሞን ፥ አንድ ፡ ያነበበውን ፡ ሰው ፡ አግኝቼ ፡ ስለ ፡ መጽሐፉ ፡ አስተያየቱን ፡ ስጠይቀው ፡— "እውነት ፡ ለመናገር ፥ ግል-ታሪክን ፡ ማንበብ ፡ አይጥመኝም ፤ ምክንያቱም ፥ ልክ ፡ ወደ ፡ ሰርግ ፡ ቤት ፡ እንደሚኼድ ፡ ሰው ፥ ተታጥቦ ፡ እና ፡ ተስተካክሎ ፣ የክት ፡ ልብሱን ፡ ለብሶ ፣ አምሮ ፡ ይታይበታል ። ታዲያ ፥ እውነቱን ፡ ማን ፡ ይንገረን ፦ በዚህ ፡ ምክንያት ፥ ብዙ ፡ አልተደሰትኩበትም" ፡ ዐለኝ ።

ስለ ፡ ግል-ታሪክ ፡ እንዲህ ፡ ቍርጥ ፡ ያለ ፡ አቋም ፡ በቃል ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ መስማቴ ፡ ነበርና ፥ ገረመኝ ።

ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፥ መጽሐፉ ፡ እኔም ፡ እጅ ፡ ገባና ፥ አነበብኹት ። ከኢትዮጵያ ፡ በልጅነት ፡ ዕድሜ ፡ በመውጣቴ ፥ ስለ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ያለኝ ፡ ግንዛቤ ፡ እጅግ ፡ ያነሰ ፡ በመኾኑ ፥ ከሸማግሌዎች ፡ እና ፡ ከመጻሕፍት ፡ የተቻለኝን ፡ ያኽል ፡ የጐደለኝን ፡ ዕውቀት ፡ ለማሟላት ፡ ዘወትር ፡ እጣጣራለኹ ።

ነፍሳቸውን ፡ ይማርና ፥ አባቴ ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፥ የሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እንደራሴ ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፡ (1962-1964 ፡ ዓ.ም.) ፡ በክረምት ፡ ወራት ፥ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ሲዘጋ ፥ ከእኅቶቼ ፡ እና ፡ ከወንድሞቼ ፡ ጋራ ፡ ከዐዲስ ፡ አበባ ፡ ወደሲዳሞ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ ሀዋሳ ፡ አባታችን ፡ ዘንድ ፡ ከእናታችን ፡ ከወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ እየኼድኩ ፡ ለኹለት ፡ ተከታታይ ፡ ክረምቶች ፡ ኖሬባት ፥ ነዋሪዋን ፡ እና ፡ መልክአ ፡ ምድሯን ፣ ውበቷን ፡ እና ፡ ልምላሜዋን ፥ በልጅነት ፡ አእምሮዬ ፡ በመጠኑ ፡ መዝግቤያቸዋለኹ ።

ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ ደግሞ ፡ በዚያው ፡ ዘመን ፡ የሲዳሞ ፡ ምክትል ፡ እንደራሴ ፡ ነበሩና ፥ ከመጽሐፋቸው ፡ አንዳንድ ፡ ከአባቴ ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ የሰማኋቸውን ፡ ታሪኮች ፡ ዝርዝር ፡ ኹኔታዎች ፡ አገኝባቸው ፡ ይኾናል ፡ በሚል ፡ መጠነኛ ፡ ጕጕት ፡ መጽሐፋቸውን ፡ ማንበብ ፡ ዠመርኩ ።

በዚህ ፡ በምታነቡት ፡ ጽሑፍ ፡ የደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድን ፡ መጽሐፍ ፡ ይዘት ፡ ባጠቃላይ ፡ ለማተት ፡ አልተነሣኹም ። የዚህ ፡ ጽሑፌ ፡ ዋና ፡ ዐላማ ፥ መጽሐፉን ፡ በወፍ-በረር ፡ በመቃኘት ፥ አንባብያን ፡ ምናልባት ፡ የማያውቁት ፡ እና ፡ ደራሲውም ፡ የከተቱት ፡ ወይ ፡ የሰወሩት ፡ ወይም ፡ ደግሞ ፡ ያዛቡት ፡ አባቴን ፡ የሚመለከት ፡ ታሪካዊ ፡ ቁም ፡ ነገር ፡ ቢኖር ፥ ባሉኝ ፡ ማስረጃዎች ፡ መሠረት ፡ ትኽክለኛውን ፡ ታሪክ ፡ ለትውልድ ፡ ለመጠቈም ፡ ይኾናል ። በተለይ ፡ ደግሞ ፥ ደራሲው ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፥ በሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ አንጻር ፡ የአፍ-ዕላፊ ፡ የሚመስሉ ፡ ቃላትን ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ የተሳሳቱም ፡ የተዛቡም ፡ ታሪኮችን ፡ ዐልፎ ፡ ዐልፎ ፡ ስላሰፈሩ ፥ በጊዜ ፡ ትኽክለኛ ፡ ምንነታቸው ፡ ተለይቶ ፡ እንዲታወቅ ፡ እና ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጡ ፡ የታሪክ ፡ ተመራማሪዎች ፡ እውነተኛውን ፡ ታሪክ ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

እንዲደርሱበት ፡ ለማመልከትም ፡ ጭምር ፡ ነው ። *"ወደ ፡ ፊት ፡ የሚመጡ ፡ የታሪክ ፡ ተመራማሪዎች"* ፡ ያልኩበት ፡ ምክንያት ፥ ዛሬ ፡ የታሪክ ፡ ተመራማሪዎች ፡ የሉም ፡ ለማለት ፡ ሳይኾን ፥ ቢኖሩም ፡ እንኳ ፥ ያለው ፡ ፀረ-ሀገር ፡ ሥርዐት ፡ ታሪክን ፡ የሚቀብሩትን ፡ እያገነነ ፣ ታሪክን ፡ የሚከሥቱትን ፡ የሚቀብር ፡ መኾኑ ፡ ስለሚታወቅ ፡ ነው ።

ደራሲው ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፥ የቤተሰቦቻቸውን ፡ አመጣጥ ፣ የትውልዳቸውንም ፡ ሐረግ ፡ እና ፡ አወራረድ ፥ እንዲሁም ፡ ጠቅላላውን ፡ የዕለት ፡ ተዕለት ፡ የኑሮ ፡ ኹኔታን ፡ ያወሡበት ፡ ኹሉ ፥ ኢትዮጵያ ፡ በ20ኛው ፡ ምእትያ ፡ መባቻ ፡ ላይ ፡ በተለይ ፡ በሰሜን ፡ ሐረርጌ ፡ በምን ፡ ዐይነት ፡ የለውጥ ፡ ኺደት ፡ ውስጥ ፡ እንደ ፡ ነበረች ፡ የሚያሳይ ፡ ታሪካዊ ፡ መዝገብ ፡ ስለ ፡ መኾኑ ፡ ጥርጥር ፡ የለውም ። ወደ ፡ ዐዲስ-አበባም ፡ መጥተው ፡ የኹለተኛ ፡ ደረጃ ፡ እና ፡ የከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ትምህርታቸውን ፡ አጠናቅቀው ፡ ወደ ፡ መንግሥታዊ ፡ አገልግሎት ፡ ያመሩበት ፥ በመንግሥታዊ ፡ አገልግሎትም ፡ ያለፉባቸው ፡ ውጣ-ውረዶች ፡ ኹሉም ፡ በእየመልካቸው ፡ የእየዘመኑን ፡ የኢትዮጵያን ፡ እውን ፡ የሚያስገነዝቡ ፡ መዝገቦች ፡ ናቸው ፤ መግቢያው ፡ ላይ ፡ ያመለከትኩት ፡ አስተያየት ፡ እንደተጠበቀ ፡ ኾኖ ።

ባለመታደል ፥ በዘመናችን ፡ የሚታተሙ ፡ የዐማርኛ ፡ መጻሕፍት ፡ የሚያሳይዋቸው ፡ ደካማ ፡ ጐኖች ፡ ኹሉ ፡ በደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድም ፡ መጽሐፍ ፡ ጐልተው ፡ ይታያሉ ። የፊደል ፡ ነገር ፡ አይወራም ፤ እጅ ፡ እና ፡ እግሩ ፡ ተሰባብረው ፡ ገብተውበታል ። ዐማርኛውም ፡ እጅግም ፡ ነው ። የሚደንቀው ፡ ነገር ፥ ደራሲው ፡ በሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ አንጻር ፡ ከሚቃጧቸው ፡ ነቀፋዎች ፡ አንዱ ፥ ዤኔራሉ ፡ በሲዳሞ ፡ እንደራሴነታቸው ፡ ዘመን ፥ በጠቅላይ ፡ ግዛቱ ፡ ጽሕፈት-ቤቶች ፡ ኹሉ ፡ የሚጻፉ ፡ ደብዳቤዎች ፡ እና ፡ ሰነዶች ፡ ፊደላቸው ፡ እየታረመ ፡ እንዲወጣ ፡ በሚል ፡ ያስተላለፉትን ፡ ቀና ፡ ሐሳብ ፡ ነበር ። ደራሲው ፡ በመጽሐፋቸው ፡ አርእስት ፥ በንኡስ-አርእስትነት ፡ *"ለሀገሬ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እና ፡ ለወገኖቼ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ዕ/እድገት ፡ የነበረኝ ፡ የሥራ ፡ ጥማት"* ፡ ብለው ፡ እንዳልጻፉ ፥ ለልማት ፡ መሠረቱ ፡ የኾነውን ፡ የፊደል ፡ መቃናትን ፡ *"አገልግሎትን ፡ ያጓትታል"* ፡ በሚል ፡ ስንፍናን ፡ በሚመስል ፡ ምክንያት ፡ መቃወማቸው ፡ በራሱ ፡ መወልገድ ፡ ኾኖ ፡ ይታያል ። መመሪያውን ፡ ተከትለውት ፡ ቢኾን ፡ ኖሮ ፥ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ምንኛ ፡ በጠቀማቸው ፡ ነበር ። ይህ ፡ መለገማቸው ፥ ከ50 ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፡ ራሳቸው ፡ በማስሊያ ፡ የለቀሙትን ፡ መጽሐፋቸውን ፡ እንዲህ ፡ በድሎት ፡ ሲታይ ፡ ላስትዋለው ፡ ኹሉ ፡ ትምህርት ፡ ይኾናል ።

ያማርኛ ፡ ፊደልን ፡ በማረም ፡ ረገድ ፡ የታየው ፡ የፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ ተቃውሞ ፡ እና ፡ መወልገድ ፥ ከዠርባቸው ፡ ከበድ ፡ ያለ ፡ ምክንያት ፡ ያነሣሣው ፡ ሠቀቀን ፡ እንደ ፡ ነበረባቸው ፡ ለጥቀን ፡ የምናያቸው ፡ ጉዳዮች ፡ ያረጋግጡልናል ።

የመዠመሪያው ፡ ጉዳይ ፡ ወደ ፡ ግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ፡ ይመልሰናል ። በዚህ ፡ ዕለት ፡ የኢትዮጵያ ፡ የሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፥ ማለት ፥ የሕግ ፡ መምሪያ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ እና ፡ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባላት ፡ በጋራ ፡ ኾነው ፡ *"የአኵስም ፡ ሐውልትን ፡ እና ፡ ቅርሳቅርሶችን ፡ የማስመለስ ፡ ውሳኔ"*ን [1] ፡ በሙሉ ፡ ድምፅ ፡ አጽድቀዋል ።

የውሳኔውን ፡ ሐሳብ ፡ ያነቁት ፡ የወሎው ፡ የሕዝብ ፡ እንደራሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ ዐመዴ ፡ ለማ ፡ ቢኾኑም ፥ ሐሳቡን ፡ ደግፈው ፡ የውሳኔውን ፡ ረቂቅ ፡ በማርቀቅ ፡ እና ፡ ለሙሉ ፡ ድምፅ ፡ ውሳኔ ፡ በማብቃት ፡ ረገድ ፡ ዋናውን ፡ ሚያ ፡ የዋሉት ፡ በወቅቱ ፡ የሕግ ፡ መዋሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ የነበሩት ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ናቸው ።

የውሳኔው ፡ ዋና ፡ ሐረግ ፡ እንዲህ ፡ ይላል ፦

> ***"የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡***
> ***መንግሥት ፥ ኢጣልያ ፡ በውል ፡***
> ***ረገድ ፡ የሚገባት ፡ እና ፡***
> ***የምታከብረውም ፡ ቋንቋ ፡ ጭንቅ ፡***

1 http://www.slttunhzb.net/IHaSA_SH_2011-003_TAA.pdf


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

*ወይም ፡ የጥቅም ፡ ግዴታ ፡ ብቻ ፡ መኾኑን ፡ አምኖ ፡ እና ፡ የአባሎቹን ፡ አስተያየት ፡ ኹሉ ፡ በዚሁ ፡ እውነት ፡ እና ፡ በሐውልቱ ፡ መመለስ ፡ ብልጫ ፡ ላይ ፡ ብቻ ፡ አስተባብሮ ፤*

*ሀ ፤ በዜጋ ፡ መሸጋገር ፡ ረገድ ፥ በመጪዎች ፡ ላይ ፡ በር ፡ እስከ ፡ መዝጋት ፡ ብቻ ፡ ሳይኾን ፥ ነዋሪዎቹንም ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማስወጣት ፥ በጥሪት ፡ መስከ ፡ ላይ ፡ ደግሞ ፡ የንግድ ፡ መሰዋወጥን ፡ እስከ ፡ ማቆምና ፥ መደምደሚያውን ፥ በዲፕሎማሲ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ግንኙነትን ፡ ፈጽሞ ፡ እስከ ፡ ማቋረጥ ፡ ድረስ ፡ ተረማማጅ ፡ በሚኾን ፡ የጭቈና ፡ ዘዴ ፡ በግልጽና ፡ በማይቋረጥ ፡ አደራረግ ፡ በመጠቀም ፥ የአኵስም ፡ ሐውልት ፡ እና ፡ ከርሱም ፡ ጋራ ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ መታሰቢያዎች ፡ በስድስት ፡ ወሮች ፡ ውስጥ ፡ ወደእየነበሩበት ፡ ስፍራ ፡ እንዲመለሱ ፡ እንዲያደርግ ፡ ያስፈልጋል ፡ ሲል ፡ ወስኖ ፤*

*ለ ፤ ይህ ፡ ሐውልት ፡ እና ፡ የሚጠቀሱት ፡ ታሪካውያን ፡ ቅርሶች ፡ ኹሉ ፡ እስከ ፡ ተመለሱና ፥ ከእነርሱም ፡ መመለስ ፡ ጋራ ፡ ዐብሮ ፡ የሚመለሰው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ክብር ፡ ተሠይሞ ፥ የኹለቱ ፡ ሀገሮች ፡ ወዳጅነት ፡ በንጹሕ ፡ መንፈስ ፡ ላይ ፡ ከመመሥረቱ ፡ በፊት ፥ የዳበረ ፡ ፍቅር ፡ መገለጫ ፡ የኾነው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ጕብኝት ፡ ክብር ፡ ቀድሞ ፡ እንዳይሰጣት ፥ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ኢጣልያ ፡ አገር ፡ መኼድ ፡ እስከዚህ ፡ ፍጻሜ ፡ ድረስ ፡ እንዲዘገይ ፡ ያሳስባል ። "*

የሥልጣን ፡ ተገቢነት ፡ በነበረው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በ 1960 ፡ ዓ.ም. ፡ የተወሰነ ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ እስከ ፡ ዛሬ ፡ ድረስ ፡ በሕግ ፡ የጸና ፥ ጥሶት ፡ የሚራመደውም ፡ ኹሉ ፡ በሕግ ፡ የሚጠየቅበት ፡ ውሳኔ ፡ ነው ። ኾኖም ፥ ገና ፡ በ 1963 ፡ ዓ.ም. ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ይህን ፡ ክልክል ፡ ተራምደው ፡ ኢጣልያን ፡ ሲጐበኙ ፥ ራሳቸውን ፡ ከሕግ ፡ በላይ ፡ አድርገው ፡ ቢኾንም ፡ ቅሉ ፥ ሕግን ፡ መጣሳቸውን ፡ ታሪክ ፡ ሲያስታውሰው ፡ ይኖራል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ኹሉ ፥ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ እጥርስ ፡ ውስጥ ፡ ገብተው ፡ እንደ ፡ ነበር ፡ ልብ ፡ ይሏል ።

ቀደም ፡ ብሎ ፥ *"ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ የዝግግኖች ፡ ማኅበር"* ፡ በሚል ፡ ስም ፡ ባዲስ ፡ ደንብ ፡ ዳግመኛ ፡ የተዋቀረው ፡ ያርበኞች ፡ ማኅበር ፥ ከ 1954 ፡ ዓ.ም. ፡ አንሥቶ ፡ የሚመራው ፡ በመላ ፡ አባላቱ ፡ በተሠየመው ፡ የሥራ ፡ አመራር ፡ ደርግ [2] ፡ ነበር ፤ የአመራር ፡ ደርጉም ፡ የመዠመሪያው ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ናቸው ። ጥር ፡ 10 ፡ ቀን ፡ 1958 ፡ ዓ.ም. ፡ ግን ፥ ከ*"ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ የዝግግኖች ፡ ማኅበር"* ፡ መተዳደሪያ ፡ ደንብ [3] ፡ ውጪ ፥ በልጅ ፡ እንዳልካቸው ፡ መኰንን ፡ የተመራ ፡ ተቀናቃኝ ፡ ቡድን ፡ በጸጥታ ፡ ኀይሎች ፡ ድጋፍ ፡ *"ሕጋዊው ፡ የዝግግኖች ፡ ማኅበር ፡ እኛ ፡ ነን"* ፡ የሚል ፡ ማስታወቂያን ፡ በማወራኛ ፡ ተቋማት ፡ አማካይነት ፡ ይፋ ፡ በማውጣት ፥ የማኅበሩ ፡ ሥራ ፡ እንዲታጐል ፣ ጽሕፈት ፡ ቤቱም ፡ በጸጥታ ፡ ኀይሎች ፡ እንዲዘጋ ፡ ተደረገ ። የተደረገበትም ፡ ዋነኛ ፡ ምክንያት ፥ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ በሕጋዊ ፡ እና ፡ በግልጽ ፡ አሠራራቸው ፡ እሕዝብ ፡ ዘንድ ፡ ያገኙት ፡ እያደር ፡ የሚዳብር ፡ ተሰሚነት ፡ እና ፡ ተቀባይነት ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡

2 <u>ደርግ</u> ፤ ወይም ፡ ድርገት ፥ "ኮሚቴ" ። (ደርግ ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ "ኮሚቴ" ፡ የሚለውን ፡ የፈረንሳይኛ ፡ ቃል ፡ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ በገቢር ፡ የተካው ፡ በ 1954 ፡ ዓ.ም. ፡ ታድሶ ፡ በጸደቀው ፡ እና ፡ በ 1956 ፡ ዓ.ም. ፡ ከመንግሥት ፡ ሕጋዊ ፡ ዕውቅናን ፡ ባገኘው ፡ በ*"ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሀገራዊ ፡ የዝግግኖች ፡ ማኅበር"* ፡ ደንብ ፡ ነው ። ካ 10 ፡ ዓመታት ፡ በኋላ ፥ በ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ የተቋቋመው ፡ ወታደራዊ ፡ ደርግ ፥ "ደርግ" ፡ የሚለውን ፡ ቃል ፡ በመጥፎ ፡ ግብሩ ፡ ስለ ፡ በከለው ፥ ዛሬ ፥ ከ"ደርግ" ፡ ይልቅ ፡ "ድርገት" ፡ የሚለው ፡ ቃል ፡ ይበልጥ ፡ ይዘወተራል ።

3 የጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ዝግግኖች ፡ ማኅበር ፡ ደንብን ፡ ⓚ ፦ slttunhzb.net/IHaSA_SH_2016-003_medbel.pdf ላይ ፡ ይመለከቷል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

እንዲሁም ፡ የጸጥታ ፡ አማካሪዎቻቸውን ፡ ስላሠጋቸው ፡ ብቻ ፡ ነበር ። ዤኔራሉም ፡ ወዲያው ፡ ከዐዲስ-አበባ ፡ እንዲርቁ ፡ ስለ ፡ ተፈለገ ፥ በስሜን-እና-በጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ተብለው ፡ ከስምንት ፡ ዓመት ፡ በፊት ፡ ተሹመው ፡ የነበሩት ፡ ሰው ፥ ደረጃቸው ፡ ዝቅ ፡ ተደርጎ ፥ የሲዳሞ ፡ "እንደራሴ" ፡ ተብለው ፡ በ 1962 ፡ ዓ.ም. ፡ መዠመሪያ ፡ ላይ ፡ ተሾሙ ። ወረድ ፡ ብለን ፡ እንደምናየው ፥ የሲዳሞ ፡ ሹመታቸው ፡ ወደ ፡ ታቀደላቸው ፡ ግድያ ፡ የሚወስዳቸው ፡ ምክንያት ፡ ነበር ፤ ነገር ፡ ግን ፥ እግዚአብሔር ፥ በማይመረመር ፡ ጥበቡ ፥ የመትረፊያቸው ፡ ምክንያት ፡ አደረገው ።

ሐተታውን ፡ የያዝነው ፡ መጽሐፍ ፡ ደራሲ ፡ (በወቅቱ ፡ ፊታውራሪ ፡ የነበሩት) ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፥ ከሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ጋራ ፡ የነበራቸው ፡ የሥራ ፡ ሱታፌ ፡ "ሀ" ፡ የተባለው ፡ በዚሁ ፡ በ 1962 ፡ ዓ.ም. ፡ ነው ። ፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ የሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ምክትል ፡ እንደራሴ ፡ ኾነው ፡ በዚያው ፡ ሰሞን ፡ ተሹመዋል ። ነገር ፡ ግን ፥ እስከዚህኛው ፡ ሹመታቸው ፡ ድረስ ፡ በሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የወላይታ ፡ (በቀድሞ ፡ ስሙ ፥ ወላሞ) ፡ አውራጃ ፡ ገዥነት ፡ ለ 7 ፡ ዓመታት ፡ አገልግለዋል ። እመጽሐፋቸው ፡ ምዕራፍ ፡ 11 ፡ ላይ ፡ በዝርዝር ፡ እንዳሰፈሩት ፥ በርከት ፡ ያለ ፡ የልማት ፡ ሥራን ፡ በአውራጃው ፡ አስፈጽመዋል ።

ሲዳሞ ፡ እጅግ ፡ ለም ፡ እና ፡ በተፈጥሮ ፡ የበለጸገ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በዚያ ፡ ዘመንም ፡ እንኳ ፥ ኢትዮጵያውያንም ፡ ኾኑ ፡ የውጭ ፡ ዜግነት ፡ ያላቸው ፡ አልሚዎች ፡ በተለይ ፡ ይረባረቡበት ፡ ነበር ፤ ያንኑ ፡ ያኽል ፡ ሙስናም ፡ ተስፋፍቶበት ፥ እውነተኛ ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ አገር ፡ አፍቃሪዎችን ፡ ኹሉ ፡ ያስቈጭ ፡ ነበር ።

ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ የሲዳሞ ፡ እንደራሴ ፡ ተብለው ፡ መሾማቸው ፡ እንደ ፡ ተሰማ ፥ በዝና ፡ አሚያውቃቸው ፡ ሰው ፡ ዘንድ ፥ በተለይ ፡ ደግሞ ፡ እ·ብዙ ፡ ተበዳይ ፡ ዘንድ ፡ የመሰማት ፡ ተስፋን ፡ ጫረ ። ከእነዚህ ፡ አንዱ ፥ አቶ ፡ አክሎግ ፡ ዘለቀ ፡ የተባሉ ፥ ኑሯቸውን ፡ እሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ያደረጉ ፡ የዤኔራሉ ፡ የቅርብ ፡ ዘመድ ፥ ዘወትር ፡ በሚያዩት ፡ የሥልጣን ፡ ብልግና ፡ እጅግ ፡ ይንገበገቡ ፡ ነበርና ፥ በትርፍ ፡ ጊዜያቸው ፡ የሥነ ፡ ጽሑፍ ፡ ልምዳቸውን ፡ ያዳበሩ ፡ ደራሲም ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፥ መንገብገባቸውን ፡ ሚያዝያ ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1962 ፡ ዓ.ም. ፡ በተቀኙት ፡ እና ፡ ላዲሱ ፡ አገረ ፡ ገዥ ፡ ለሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ በላኩላቸው ፡ ግጥማቸው ፡ ትዝብታቸውን ፡ እና ፡ ሠቀቀናቸውን ፡ እንዲህ ፡ ሲሉ ፡ በቅኔ ፡ ገልጸዋቸዋል [4] ፡—

*"[...]*

*ለምለሙ ፡ ሲዳሞ ፥ እንኳን ፡ ደስ ፡ ዐለኽ!*
*ጨልሞብኽ ፡ ነበር ፤ አኹን ፡ ነጋልኽ ።*
*እስካኹን ፡ ሲዳሞ ፡ ምንድን ፡ ነው ፡ የኾንከው ፡ ፧*
*ኑሮኽ ፡ እንዴት ፡ ነበር ፧ እኔ ፡ ነኝ ፡ የማውቀው ።*
*ለምን ፡ እኔ ፡ ብቻ ፧ ማንም ፡ ይመስክር ፥*
*እንዴት ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ ያንተ ፡ አስተዳደር ።*
*በክፍል ፡ በክፍሉ ፥ በእየተዋረደ ፥*
*በብዙ ፡ ሺሕ ፡ ገንዘብ ፥ በብዙ ፡ ፓውንድ ፥*
*ኮንትራት ፡ ተሰጥተኽ ፡ እንደራስ ፡ ሑዳድ ፥*
*አምርተኽ ፡ አትበላ ፥ አስብተኽ ፡ አታርድ ፥*
*ዳኝነት ፡ ተነፍገኽ ፡ ኑሮኽ ፡ ሥር ፡ በግድ ።*
*[...]"*

በተለይ ፡ በሀዋሳ ፡ እና ፡ በሶዶ ፡ (ወላይታ) ፡ ከተማዎች ፥ በልማት ፡ ስም ፥ ብዙ ፡ የድኻ ፡ ርስት ፡ አላግባብ ፡ እየተነጠቀ ፡ ለባለሀብቶች ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበርና ፥ ዤኔራሉ ፡ የሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አስተዳደር ፡ ሥራቸውን ፡ ሲዠምሩ ፥ "አላግባብ ፡ የተወሰደብኝ ፡ ርስቴ ፡ ይመለስልኝ" ፡ የሚል ፡ በርካታ ፡ አቤቱታ ፡ ተከማችቶ ፡ ጠበቃቸው ። ለጕዳዩ ፡ ዐዲስ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፥ ከሀገሩ ፡ ሽማግሌዎች ፡ ጋራ ፡ አጥንተው ፡ እና ፡ መክረው ፥ ትኽክለኛውን ፡ ኹኔታ ፡ ከተረዱ ፡ በኋላ ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥታዊው ፡ መንግሥት ፡

4 የአቶ ፡ አክሎግ ፡ ዘለቀ ፡ ግጥም ፡ ሙሉ ፡ ይዘት ፡ በሥልጡንሕዝብና ፡ መዜንው ፡ ቀ·.2018-003 ፥ "ከመቃብር ፡ በላይ" ፡ በተሠኘው ፡ ዐምድ ፡ ላይ ፡ ወጥቷል ፡— slttunhzb.net/IHaSA_SH_2018-003_KB.pdf


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

ሕግ ፡ እና ፡ ዐዋጅ ፡ መሠረት ፥ እያንዳንዱን ፡ አቤቱታ ፡ በመስማት ፡ በሥልጣናቸው ፡ የሚወሰነውን ፡ ኹሉ ፡ በሕጉ ፡ እና ፡ በዐዋጁ ፡ መሠረት ፡ ፍትሐዊ ፡ የኾነውን ፡ ውሳኔ ፡ እያስፈጸሙ ፡ ቀጠሉ ።

ይህ ፡ ቀጥተኛ ፣ ሕጋዊ ፡ እና ፡ ቀልጣፋ ፡ አሠራራቸው ፡ በሕዝብ ፡ የተወደደውን ፡ ያኽል ፥ ሳይውል ፡ ሳያድር ፡ ከተወሰኑ ፡ ጥቅመኞች ፡ ከባድ ፡ ተቃውሞን ፡ አስነሣባቸው ። በተለይ ፡ በልዕልት ፡ ተናኝ-ወርቅ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ አላግባብ ፡ ከሕዝብ ፡ የተነጠቁ ፡ ርስቶች ፡ ለሕጋውያን ፡ ባለርስቶቹ ፡ እንዲመለሱ ፡ ባስደረጉ ፡ ጊዜ ፥ ከንጉሣዊው ፡ ቤተሰብ ፡ ጋራ ፡ በቀጥታ ፡ የሚያጋጫቸው ፡ ኾነ ።

በሌላ ፡ በኩል ፥ የውጭ ፡ አልሚዎች ፡ በብዙ ፡ ሚልዮን ፡ ብር ፡ የሚገመት ፡ ሀብታቸውን ፡ ለልማት ፡ ለማፍሰስ ፡ ከመንግሥት ፡ ባገኙት ፡ ፈቃድ ፡ መሠረት ፥ ለልማት ፡ ሲባል ፡ የሕዝብ ፡ ርስት ፡ በተመጣጣኝ ፡ የካሳ ፡ ክፍያ ፡ እየተወሰደ ፡ ለአልሚ ፡ ይሰጣል ፡ የሚለውን ፡ ዐዋጅ ፡ ተከትሎ ፥ የዐያሌ ፡ ሰው ፡ ርስት ፡ አላንዳች ፡ የካሳ ፡ ክፍያ ፡ እየተነጠቀ ፡ ቀደም ፡ ሲል ፡ ለአልሚዎች ፡ ተሰጥቶ ፡ ነበር ።

አገረ ፡ ገዢው ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴም ፥ በዚህ ፡ ረገድ ፥ ዕለት ፡ በዕለት ፡ የሚቀርብላቸውን ፡ ጕዳይ ፡ ሲፈቱ ፥ ከሕጉ ፡ እና ፡ ከኅሊናቸው ፡ በቀር ፡ የሚጠነቀቁለት ፡ አልነበረም ። ከዠርባ ፡ ይህ ፡ ሥራ ፡ የሚያስከትልባቸውን ፡ አደጋ ፡ ቢገምቱትም ፡ እንኳ ፥ ፈርተውት ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አላሉም ።

እንደተጠበቀውም ፥ እላይ ፡ ከጠቀስናቸው ፡ ኹለት ፡ አግጣጫዎች ፡ ከባድ ፡ አደጋ ፡ መጣባቸው ።

አንደኛው ፡ አግጣጫ ፡ ከንጉሣዊው ፡ ቤተሰብ ፡ ኾነ ። የልዕልት ፡ ተናኝ-ወርቅ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ የሲዳሞ ፡ ርስት ፡ በበላይ ፡ ኀላፊነት ፡ የሚያስተዳድሩት ፡ እና ፡ ዶባ ፡ ከተባለው ፡ የሸዋ ፡ አካባቢ ፡ በመወለድ ፡ ከቀዳማዊ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ አባት ፡ አባት ፡ የሚዘመዱት ፡ ደጃዝማች ፡ ብርሃነ-መስቀል ፡ ወልደ-ሥሳሴ ፡ ናቸው ። ከሲዳሞ ፡ ምክትል ፡ እንደራሴ ፡ ከፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድም ፡ ጋራ ፡ በዚሁ ፡ የዘር ፡ ግንድ ፡ በቅርብ ፡ ይዘመዳሉ ።

ደጃዝማች ፡ ብርሃነ-መስቀል ፡ ወልደ-ሥሳሴ ፡ በስብቅልነታቸው ፡ እና ፡ በግልጽነታቸው ፡ ይታወቃሉ ። ከሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴም ፡ ጋራ ፡ ገነት ፡ ሆሎታ ፡ ጦር ፡ ትምህርት ፡ ቤት ፡ ዐብረው ፡ ተምረው ፥ ዤኔራሉ ፡ በማዕርግ ፡ የበላያቸው ፡ ቢኾኑም ፡ ቅሉ ፥ ዐብረው ፡ ተመርቀዋል ። በዚህ ፡ ምክንያት ፥ በኹለቱ ፡ መኰንኖች ፡ መኻከል ፡ የቈየ ፡ ወዳጅነት ፡ አለ ። ነገር ፡ ግን ፥ ጥቅም ፡ የማይሽረው ፡ ወዳጅነት ፡ ጥቂት ፡ ነውና ፥ የግቢ ፡ ምክትል ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝማች ፡ ብርሃነ-መስቀል ፡ ወልደ-ሥሳሴ ፡ በሚያልፍ ፡ ጥቅም ፡ ተደልለው ፡ ኖሮ ፥ በእንደራሴው ፡ በሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ላይ ፡ ተነሣሡባቸው ። ታሪኩን ፡ ራሳቸው ፡ አባቴ ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ደጋግመው ፡ አጫውተውኛል ፤ ከእናቴ ፡ ከወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ-ሥላሴም ፡ ጋራ ፡ ጕዳዩ ፡ በተነሣ ፡ ቍጥር ፡ እንጨዋወተዋለን ። ታሪኩ ፡ እንዲህ ፡ ነው ፤

አንድ ፡ ቀን ፥ ደጃዝማች ፡ ብርሃነ-መስቀል ፡ ወልደ-ሥሳሴ ፡ ሀዋሳ ፡ ሐይቅ ፡ ዳር ፡ ወደሚገኘው ፡ የአገረ ፡ ገዢው ፡ መቀመጫ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ሲከንፉ ፡ ይመጣሉ ። ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ እንዳገኟቸውም ፦ "ዤኔራል ! አንተን ፡ እኮ ፡ እግዚአብሔር ፡ ይወድኻል !" ይሏቸዋል ። ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴም ፡ ተገርመው ፦ "እንዴት ፧ ምን ፡ ማለትኽ ፡ ነው ፧" ሲሉ ፡ ይጠይቋቸዋል ። የልባቸውን ፡ በመናገር ፡ የሚታወቁት ፡ ደጃዝማች ፡ ብርሃነ-መስቀል ፡ ወልደ-ሥሳሴም ፡ ሲመልሱ ፦ « በልዕልት ፡ ተናኝ-ወርቅ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ርስት ፡ ጕዳይ ፡ ብታስቸግረኝ ፡ ጊዜ ፥ ለጃንሆይ ፡ አቤት ፡ ዐልኹ ፤ ጃንሆይም ፡ አቤቱታዬን ፡ ሰሙና ፦ "ታዲያ ፥ ነጋ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነው ፤ ርሱን ፡ ማስወገድ ፡ ምን ፡ ያቅትኻል ፧" ዐሉኝ ፥ እኔም ፦ "አአይ ፡ ጃንሆይ ፥ እኔም ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ነኝ ፤ በየትኛው ፡ ዐቅሜ ፡ ነው ፡ አንድ ፡ አገረ ፡ ገዥን ፡ የማስወግደው ፧ ስላቸው ፦ "ላንድ ፡ ሰው ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ መች ፡ አነሰው ፧" ዐሉኝ ፤


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

ወዲያው ፡ ዞር ፡ ብለው ፥ እልፍኝ ፡ አስከልካያቸውን ፦ "አንድ ፡ ሽጉጥ ፡ እንድትሰጠው!" ብለው ፡ አዘዙት ፡ እና ፦ "ፈቅጄልኻለኹ!" ዐሉኝ ። እኔም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ፈቃድ ፡ እና ፡ ሽጉጥ ፡ ተቀብዬ ፥ ለጥ ፡ ብዬ ፡ እጅ ፡ ነሥቼ ፡ ወጣኹ ። ከዚያም ፥ ይህን ፡ ንጉሣዊ ፡ መልክት ፡ እንዲፈጽምልኝ ፡ አንዱን ፡ ታማኝ ፡ አሽከሬን ፡ ሽጉጡን ፡ አስረክቤው ፡ እንዲገድልኽ ፡ ላክኹት ። ይህም ፡ አሽከር ፦ "የተቀበልኩት ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ትእዛዝ ፡ ነው!" ብሎ ፡ ጕዳዩ ፡ ምንም ፡ ሳያሠጋው ፥ በሀዋሳ ፡ ከተማ ፡ በእየመጠጥ ፡ ቤቱ ፡ እየጠጣ ፥ ሞቅ ፡ ሲለውም ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ሽጉጡን ፡ እየመዘዘ ፦ *"በሽጉጥ ፡ ነው ፡ ግንባሩን ፡ ብዬ ፡ የማሰናብተው!"* እያለ ፡ እየዛተ ፤ ሌላም ፡ ቀን ፡ እንደዚሁ ፦ *"በሽጉጥ ፡ ነው ፡ ደረቱን ፡ የማፈርሰው!"* እያለ ፡ እየፎከረ ፡ ሽጉጡን ፡ ከብብቱ ፡ ዐሥር ፡ ጊዜ ፡ ሲመዝ ፡ እና ፡ መልሶ ፡ ሲከት ፥ አንድ ፡ ቀን ፥ መጠጡን ፡ አብዝቶት ፡ ኖሮ ፥ ሳያውቅ ፡ በገዛ ፡ እጁ ፡ ደረቱን ፡ በጥይት ፡ መትቶ ፡ ወዲያው ፡ ሞተ ። ነጋ ፡ ይቅር ፡ በለኝ ! ወንድሜን ፡ አስገድዬኽ ፡ ነበር ! እግዚአብሔር ፡ ግን ፡ ይወድኻል ፤ በማይመረመር ፡ ጥበቡ ፡ አተረፈኽ ። » ብለው ፡ የደረሰውን ፡ ኹሉ ፡ በዝርዝር ፡ ነገሯቸው ።

ይህ ፡ ታሪክ ፡ ልብ-ወለድ ፡ እንጂ ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ለማመን ፡ ለብዙ ፡ ሰው ፡ ሳይቸግረው ፡ እንደማይቀር ፡ ዐውቃለኹ ፤ ነገር ፡ ግን ፡ በእውን ፡ የደረሰ ፡ እና ፡ እስከዛሬም ፡ ድረስ ፡ የዐይን ፡ ምስክሮች ፡ የሚመሰክሩበት ፡ እውነተኛ ፡ ታሪክ ፡ ነው ። አንዷ ፡ ምስክር ፡ ዛሬም ፡ በሕይወት ፡ ያለችው ፡ እናቴ ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ናቸው ። የሟቹ ፡ ቤተሰቦችም ፡ ዛሬም ፡ ይኖራሉና ፥ ሊጠየቁ ፡ ይችላሉ ፤ የፖሊስ ፡ መዝገብም ፥ በሥርዐት ፡ ተይዞ ፡ እንደ ፡ ኾነ ፥ ሙሉ ፡ ዝርዝሩን ፡ ሊሰጠን ፡ ይችላል ። በበኩሌ ፥ በ 2016 ፡ ዓ.ም. ፥ ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድን ፡ ዐዲስ-አበባ ፡ ድረስ ፡ ደውዬ ፥ "ሕይወቴ" ፡ ስለተባለው ፡ ዐዲስ ፡ የወጣ ፡ መጽሐፋቸው ፡ ሳነጋግራቸው ፥ በመኻከሉ ፡ እላይ ፡ ስለ ፡ ገለጽኹት ፡ በሊ. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ላይ ፡ ስለተቃጣው ፡ የግድያ ፡ ሙከራ ፡ ታሪክ ፡ እና ፡ አሳዛኝ ፡ ፍጻሜው ፡ የሚያውቁት ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ስጠይቃቸው ፦ "ጭምጭምታ ፡ ሰምቻለኹ !" በማለት ፡ ባጪሩ ፡ መልሰውልኛል ።

ኹለተኛው ፡ የአደጋ ፡ አግጣጫ ፡ የመጣው ፡ ደግሞ ፡ "ኢንቬስተር" ፡ ከሚሏቸው ፡ አልሚዎች ፡ በኩል ፡ ኾነ ። በሚልዮን ፡ ብር ፡ የሚገመት ፡ የልማት ፡ ሥራ ፡ በሚከናወንበት ፡ ኹኔታ ፡ ኹሉ ፡ ሙስና ፡ ዐብሮ ፡ መኖሩ ፡ እና ፡ ሕዝብ ፡ መበደሉ ፡ አያጠራጥርም ። በተለይ ፡ ግን ፥ ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፥ "ሕይወቴ" ፡ በተባለው ፡ መጽሐፋቸው ፡ ከእነማስረጃው ፡ እንዳረጋገጡት ፥ አብዛኛዎቹ ፡ አልሚዎች ፡ ኢጣልያውያን ፡ ነበሩ ። እዚህ ፡ ላይ ፡ ታዲያ ፥ የግንቦት ፡ 1 ፡ ቀን ፡ 1960 ፡ ዓ.ም. ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ በአኵስም ፡ ሐውልት ፡ እና ፡ በቅርሳቅርሶች ፡ መመለስ ፡ ጕዳይ ፡ በኢጣልያውያን ፡ አልሚዎች ፡ አንጻር ፡ የጣለው ፡ እግድ ፡ ሲዳሞ ፡ ውስጥ ፡ በይፋ ፡ ተጥሶ ፡ ይታይ ፡ ነበር ።

ሊ. ፡ ጀኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፥ የሕግ ፡ መወሰኛ ፡ ምክር ፡ ቤት ፡ አባል ፡ በነበሩበት ፡ ዘመን ፥ ውሳኔውን ፡ ካረቀቁት ፡ እና ፡ ካስጸደቁት ፡ ግንባር ፡ ቀደሙ ፡ ነበሩና ፥ ከኹለት ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ በ 1962 ፡ ዓ.ም. ፡ ወደ ፡ ሲዳሞ ፡ በሀገረ ፡ ገዥነት ፡ ሲመጡ ፥ የኢጣልያውያኑ ፡ የንግድ ፡ እንቅስቃሴ ፡ እጅግ ፡ ተጧጡፎ ፡ በማየታቸው ፦ *"ይህ ፡ ኹኔታ ፡ እንዴት ፡ ተፈቀደ ፡ ?"* ብለው ፥ ዋናውን ፡ ኢጣልያዊ ፡ አልሚ ፡ አስጠርተው ፡ አነጋገሩት ። ስሙን ፡ የማልጠቅሰው ፡ ይህ ፡ ኢጣልያዊም ፥ ከመተማመኑ ፡ የተነሣ ፥ ለአገረ ፡ ገዢው ፡ ጥያቄ ፡ እንዲህ ፡ ሲል ፡ በግልጽነት ፡ መለሰ ፦ *"ሰሙ ፥ ክቡር ፡ ጀኔራል ፥"* ዐለና ፥ ከሱሪው ፡ ኪስ ፡ መሐርቡን ፡ በማውጣት ፥ *"ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፥ እንደዚህ ፡ መሐርብ ፥ እኪሳችን ፡ ከትተናቸዋል!"* ብሎ ፡ መሐርቡን ፡ እኪሱ ፡ መልሶ ፡ ከተተው ። ይህ ፡ ቃል ፥ ተጠይቆ ፡ የተናገረው ፡ እውነት ፡ እንጂ ፥ ከመሬት ፡ ተነሥቶ ፡ ለመሳደብ ፡ የተናገረው ፡ በክብረ ፡ ነክም ፡ የሚያስጠይቀው ፡ አልነበረምና ፥ ጀኔራሉ ፡ መራራውን ፡ እውነት ፡ ዋጥ ፡ አድርገው ፡ ተለያዩ ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

ብዙም ፡ ሳይቈይ ፥ በሕዝብ ፡ የቀረቡትን ፡ አቤቱታዎች ፡ ለመስማት ፡ እና ፡ በቍርጠኛ ፡ ውሳኔ ፡ ለመፍታት ፥ ሲ. ፡ ገቨኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ በሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ታጅበው ፥ በወላሞ ፡ አውራጃ ፡ ዋና ፡ ከተማ ፡ በሶዶ ፡ ሰፊ ፡ ችሎትን ፡ አስቻሉ ።

በርስት ፡ ጕዳይ ፡ የቀረቡትን ፡ አቤቱታዎች ፥ አስተዳደራዊ ፡ ውሳኔ ፡ የሚያሻቸውን ፡ በመለየት ፡ እና ፡ እዚያው ፡ እሕዝብ ፡ ፊት ፡ በመፍታት ፦

1. ፲ አላግባብ ፡ የተነጠቀው ፡ የነዋሪው ፡ ርስት ፡ ለባለርስቱ ፡ እንዲመለስ ፲
2. ፲ መሬቱ ፡ ለልማት ፡ ተፈልጎ ፥ በዐዋጁ ፡ መሠረት ፥ ለባለርስቱ ፡ ሊከፈል ፡ የሚገባው ፡ ተመጣጣኝ ፡ ካሳ ፡ እስካልተከፈለ ፡ ድረስ ፡ ርስቱ ፡ ለባለቤቱ ፡ እንዲመለስ ፡ ወሰኑ ።

በዚህ ፡ ኹሉ ፡ ጊዜ ፥ ምክትል ፡ እንደራሴው ፡ ፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፥ በመጸሐፋቸው ፡ ገጽ ፡ 396 ፡ ላይ ፡ *"ክቡር ፡ እንደራሴው ፡ ከሀዋሳ ፡ ወደ ፡ ወላይታ ፡ ሶዶ ፡ መጡ ፡ እና ፡ ጉባኤ ፡ ከፈቱብኝ"* ፡ በሚል ፡ ርእስ ፡ ክፍለ ፡ ሀገራዊውን ፡ ጕዳይ ፡ የግል ፡ ጕዳያቸው ፡ አድርገው ፡ እንደ ፡ ገለጹት ፥ እዚያው ፡ እሶዶ ፡ ከተማ ፡ እሚገኘው ፡ ቤታቸው ፡ ተቀምጠው ፥ አገረ ፡ ገዥው ፡ ካስቻሉት ፡ ችሎት ፡ አልሳተፍም ፡ ብለው ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ከቦለዱ ፡ በኋላ ፥ ታዘው ፡ ቢሳተፉም ፥ ራሳቸውን ፡ እንደ ፡ ተከሳሽ ፡ በመቍጠር ፥ በባለሥልጣኑ ፡ ረድፍ ፡ ለመቀመጥ ፡ አልወደዱም ። የሚነሣው ፡ አቤቱታ ፡ ኹሉ ፥ በተለይ ፡ የንግድ ፡ ቦታቸውን ፡ አላግባብ ፡ የተነጠቁ ፡ የሶዶ ፡ ነጋዴዎች ፡ አቤቱታ ፥ ምክትል ፡ እንደራሴ ፡ ፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድን ፡ በቀጥታም ፡ በተዘዋዋሪም ፡ ስለ ፡ ነካቸው ፥ *"... ፡ እንደራሴውን ፡ ከእነግብስብሶቻቸው ፡ እዚያው ፡ እሶዶ ፡ ከተማ ፡ እንዳሉ ፡ ትቼ ፡ ወደ ፡ ዐዲስ-አበባ ፡ መኼድ ፡ እና ፡ እቤቴ ፡ ዐርፌ ፡ መክረሙን ፡ መረጥኩ ። "* ሲሉ ፡ ጽፈዋል ።

በመጨረሻም ፥ *"... ፡ ክቡር ፡ እንደራሴው ፡ በዕለቱ ፡ የወሰኑት ፡ የሶዶ ፡ ከተማን ፡ ማስተር ፡ ፕላን ፡ የሚያፈርስ ፡ እና ፡ በፍጹም ፡ ሥራ ፡ ላይ ፡ መዋል ፡ የማይችል ፥ ሶሎል ፡ ቦኔ ፡ ይሠራው ፡ በነበረው ፡ ኢንተርናሽናል ፡ መንገድ ፡ ላይ ፡ ለሚገኙ ፡ ሰዎች ፡ ለኹሉም ፡ ግምት ፡ ይከፈል ፡ ብለው ፡ እንደ ፡ ሰጡት ፡ መሣቂያ ፡ ኾኖ ፡ እንደ ፡ ቀረው ፡ ትእዛዝ ፡ ዐይነት ፡ ነበር ። የሚያሳዝነው ፡ ነገር ፡ ግን ፥ በዚያ ፡ ዕለት ፡ በጣም ፡ ተናደው ፡ ስለ ፡ ነበር ፥ ከፍተኛ ፡ የደም ፡ ግፊት ፡ ዐድሮባቸው ፥ ሶዶ ፡ ከተማ ፡ በሚገኘው ፡ የሱዳን ፡ ኢንቲርየር ፡ ሆስፒታል ፡ ርዳታ ፡ ከተደረገላቸው ፡ በኋላ ፥ ባስቸኳይ ፡ ወደ ፡ ዐዲስ-አበባ ፡ እንደ ፡ ኼዱ ፡ ሰማኹ ። ዐዲስ-አበባም ፡ ርዳታ ፡ ቢደረግላቸው ፥ የደም ፡ ግፊታቸው ፡ ከባድ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ለንደን ፡ ኼዱ ። ..."* [ገጽ ፡ 396] ሲሉ ፥ ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ ፍርደ ፡ ገምድልነትን ፡ ከውሸት ፡ ጋራ ፡ የቀላቀለ ፡ ትረካን ፡ በጽሑፍ ፡ አስፍረውልናል ።

መዠመሪያ ፡ ነገር ፥ የመንግሥት ፡ ዐዋጅ ፡ በሚያዘው ፡ መሠረት ፡ ለሕዝብ ፡ ተገቢው ፡ ካሳ ፡ እንዲከፈል ፡ እንደራሴው ፡ ሲ. ፡ ገቨኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ውሳኔን ፡ ቢወስኑ ፡ እና ፡ ይህንም ፡ ሕጋዊ ፡ ውሳኔ ፡ ቢያስፈጽሙ ፥ ፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ ለምን ፡ ተንገበገቡ ፧ በውሳኔውስ ፡ ለምን ፡ ተሣለቁ ፧ ይህ ፡ ራሱ ፡ በሙስናው ፡ ውስጥ ፡ ነበሩበት ፡ ብሎ ፡ ለመጠርጠር ፡ ፍንጭ ፡ አይሰጥምን ፧ ለሀገር ፡ ልማት ፡ እቈረቈራለኹ ፡ ካሉ ፡ ዘንዳ ፥ የድኻው ፡ መበደል ፡ እንዴት ፡ ሳይሰማቸው ፡ ቀረ ፧

ኹለተኛ ፡ ነገር ፥ ፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ የፈጠራ ፡ ሕመምን ፡ ለሲ. ፡ ገቨኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ሊሰጧቸውስ ፡ ለምን ፡ መረጡ ፧ ሲ. ፡ ገቨኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፥ በ2000 ፡ ዓ.ም. ፡ በ90 ፡ ዓመታቸው ፡ እስካረፉበት ፡ ዘመን ፡ ድረስ ፡ የደም ፡ ግፊት ፡ የሚባል ፡ በሽታ ፡ አግኝቷቸው ፡ አያውቅም ። ነገር ፡ ግን ፥ የወላይታ ፡ ሶዶ ፡ ጉባኤን ፡ ካካኼዱ ፡ በኋላ ፥ 2ኛ ፡ የግድያ ፡ ሙከራ ፡ ተፈጽሞባቸዋል ። በዚህ ፡ ጊዜ ፥ ፊታውራሪ ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፡ ከሀዋሳ ፡ ሸሽተው ፡ ወደ ፡ ዐዲስ-አበባ ፡ ኼደዋል ።


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ የሚያማቸው ፡ አንድ ፡ ሕመም ፡ ብቻ ፡ ነበር ፥ ርሱም ፡ የጨጓራ ፡ ኩምጣጤ ፡ ወይም ፡ "ጋስትራይቲስ" ። እይርጋ-ዓለም ፡ ከተማ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ የሚሠራ ፡ አንድ ፡ የዩጎስላቪያ ፡ ሐኪም ፦ "ባንድ ፡ መርፌ ፡ የሚድን ፡ ሕመም ፡ ነው ።" በሚል ፡ የተስፋ ፡ ቃል ፡ ቀጠሮ ፡ ሰጥቷቸው ፡ ኖሮ ፥ ወደ ፡ ይርጋ-ዓለም ፡ ለመኼድ ፡ ሲሰናዱ ፥ ባልተቤታቸው ፡ ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፥ ኹኔታው ፡ አደገኛ ፡ ስለ ፡ መሰላቸው ፦ *"መርፌ ፡ መወጋት ፡ ቢቀርብዎ ፡ ይሻላል ። በታኅሣሥ ፡ 1953 ፡ ዓ.ም. ፡ ግርግር ፡ ዋዜማም ፡ እንደዚሁ ፡ ታመው ፡ መርፌ ፡ ሊወጉ ፡ ሲሉ ፥ ይቅርብዎ ፡ ብልዎ ፥ እምቢ ፡ ብለው ፡ ሐኪም ፡ መርዝ ፡ ወግቶ ፡ ሊገድልዎ ፡ ነበር ፤ ዛሬም ፡ ከዚህ ፡ የተለየ ፡ አይኾንምና ፥ ይቅርብዎ!"* ብለዋቸው ፡ ነበር ። [ርግጥ ፡ ነው ፥ ከእነብሪጋድዬ ፡ ዤኔራል ፡ መንግሥቱ ፡ ንዋይ ፡ የታኅሣሥ ፡ 1953 ፡ ዓ.ም. ፡ የዐልጋ ፡ ግልበጣ ፡ ሙከራ ፡ ጥቂት ፡ ቀናት ፡ በፊት ፥ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ለሕክምና ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ በቀጠሮ ፡ ኼደው ፥ ሐኪም ፡ መርዝ ፡ ወግቷቸው ፥ በተኣምራት ፡ ሕይወታቸው ፡ ቢተርፍም ፥ የግርግሩን ፡ ወቅት ፡ ኹሉ ፡ እልዕልት ፡ ፀሐይ ፡ ሐኪም ፡ ቤት ፡ ተኝተው ፡ በሕክምና ፡ አሳልፈዋል ።]

ካሥር ፡ ዓመት ፡ በኋላ ፥ በ1963 ፡ ዓ.ም. ፥ በይርጋ-ዓለሙ ፡ የሐኪም ፡ ቀጠሮ ፡ ዤኔራሉ ፡ ያልሠጉበት ፡ ምክንያት ፥ ሐኪሙ ፡ የዩጎስላቪያ ፡ ሰው ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ በጠላትነት ፡ መንፈስ ፡ የሚነሣሣበት ፡ ምክንያት ፡ አይኖረውም ፡ ብሎ ፡ በማመን ፡ ነበር ። ዳሩ ፡ ግን ፥ ስሕተቱ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ኾነ ። ያ ፡ የዩጎስላቪያ ፡ ሐኪም ፥ ተገዝቶ ፡ ኖሮ ፥ በቀጠሮው ፡ ቀን ፥ መርፌውን ፡ ለመውጋት ፡ የተመደበችውን ፡ ረዳት ፡ ("ነርስ") ፡ ለመድኀኒቱ ፡ ከሚፈቀደው ፡ ምጣኔ ፡ ወይም ፡ "ዶዝ" ፡ 8 ፡ ዕጥፍ ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ እንድትወጋ ፡ ያዛታል ። ርሷም ፥ ኋላ ፡ በምርመራ ፡ ስትጠየቅ ፡ እንዳረጋገጠችው ፥ *"ይህ ፡ እንዴት ፡ ይኾናል ፧ ሊገድላቸው ፡ ይችላል ፡ እኮ ፧"* ፡ ብላ ፡ ብታንገራግር ፥ *"ኀላፊነቱ ፡ የኔ ፡ ነው ፤ ያንቺ ፡ ድርሻ ፡ የታዘዝሽውን ፡ መፈጸም ፡ ብቻ ፡ ነው ።"* ሲል ፡ ያስገድዳታል ።

በታዘዘችው ፡ መሠረት ፡ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ መድኀኒቱን ፡ በ8 ፡ ዕጥፍ ፡ ምጣኔ ፡ ወጋቻቸው ። ዤኔራሉም ፥ መርፌውን ፡ እንደ ፡ ተወጉ ፥ የማጥወልወል ፡ እና ፡ የማዞር ፡ ከባድ ፡ ስሜት ፡ ሲሰማቸው ፥ ቶሎ ፡ ብለው ፡ ተነሥተው ፡ እየተንገዳገዱ ፡ ወደ ፡ መኪናቸው ፡ ኼደው ፥ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ ሀዋሳ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ተመለሱ ። እዚያም ፡ እንደ ፡ ደረሱ ፥ የተቻለውን ፡ ያኽል ፡ ለመርዙ ፡ ማብረሻ ፡ ይረዳል ፡ የተባለው ፡ ኹሉ ፡ ከተደረገላቸው ፡ በኋላ ፥ በፍጥነት ፡ ወደ ፡ ዐዲስ-አበባ ፡ በመኼድ ፥ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ፈቃድ ፥ ወደ ፡ እንግሊዝ ፡ አገር ፡ ተጕዘው ፡ ለመታከም ፡ እና ፡ ለመትረፍ ፡ በቁ ። በለንደን ፡ ከተማ ፡ ያከማቸው ፡ ዶክተር ፡ ቶምኪንዝ ፡ (Dr. Thomkins) ፡ የተባለው ፡ የዝነኛው ፡ "ሀርሌ ፡ ስትሪት" ፡ ሐኪም ፥ ሙሉ ፡ ሕክምናውን ፡ ከሰጣቸው ፡ በኋላ ፥ የመትረፋቸውን ፡ ተኣምርነት ፡ በመመስከር ፦ *"የመድኀኒቱን ፡ 8 ፡ ዕጥፍ ፡ ምጣኔ ፡ ተወግቶ ፡ ቆሞ ፡ መኼድ ፡ የሚችል ፡ ሰው ፡ የለም ፤ ልቡ ፡ ፈርሶ ፡ እመቀመጫው ፡ ላይ ፡ ቍጭ ፡ እንዳለ ፡ ይቀራል ። ይህ ፡ ፍጹም ፡ ተኣምር ፡ እንጂ ፡ በሕክምና ፡ ጥበብ ፡ ይቻላል ፡ የሚባል ፡ አተራረፍ ፡ አይደለም ። ፈቃድዎ ፡ ከኾነ ፥ ይህኑ ፡ ድምዳሜዬን ፡ በጽሑፍ ፡ አመልክቼ ፡ ልስጥዎ ።"* ብሏቸው ፡ ነበር ።

እግዚአብሔር ፡ *"አትሙት"* ፡ ያላት ፡ ነፍስ ፡ አትሞትምና ፥ ሊ. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ከዚህኛውም ፡ የግድያ ፡ ሙከራ ፡ በተኣምር ፡ ተርፈው ፡ ባስተማማኝ ፡ ጤንነት ፡ ወደ ፡ ኢትዮጵያ ፡ ተመለሱ ።

ኹሉም ፡ በኹሉ ፥ ሲዳሞ ፡ በእንደራሴነት ፡ በቈዩበት ፡ ወቅት ፥ የምናውቃቸው ፡ 3 ፡ የግድያ ፡ ሙከራዎች ፡ ተፈጽመውባቸው ፥ ከ3ቱም ፡ በእግዚአብሔር ፡ ተኣምራት ፡ ተርፈዋል ።

እስካኹን ፡ የገለጥናቸው ፡ ኹለቱ ፡ የግድያ ፡ ሙከራዎች ፡ ኹለተኛው ፡ እና ፡ ሦስተኛው ፡ ናቸው ። የመዠመሪያው ፡ የግድያ ፡ ሙከራ ፡ የተቃጣው ፥ በእንደራሴነት ፡ እሲዳሞ ፡ እንደ ፡

ገቡ ፥ ገና ፡ አንድ ፡ ወር ፡ እንኳ ፡ ሳይቈዩ ፥ በቤት ፡ አሽከርነት ፡ ከዐዲስ-አበባ ፡ ዐብሯቸው ፡ የመጣ ፡ ሰው ፥ ፈንጂ ፡ እና ፡ ማፈንጃውን ፡ የመዳብ ፡ ሽቦ ፡ በስውር ፡ ተቀብሎ ፥ በአገረ ፡ ገዢው ፡ መኪና ፡ ላይ ፡ በመጥመድ ፡ ለማፈንዳት ፡ በሚዘጋጅበት ፡ ወቅት ፡ ነበር ። ድርጊቱን ፡ ገና ፡ ሳይፈጽመው ፥ ድንገት ፡ አንድ ፡ ሌሊት ፥ ጸጸቱ ፡ አሸንፎት ፡ ሳይኾን ፡ አይቀርም ፥ ይህ ፡ ሠራተኛ ፡ ራሱን ፡ ለማጥፋት ፥ ዐንገቱን ፡ በገመድ ፡ ዐንቆ ፡ እዛፍ ፡ ላይ ፡ ተንጠልጥሎ ፡ ሲወራጭ ፡ የሰሙ ፡ አለቃ ፡ ባሕሩ ፡ የተባሉ ፡ ሀዋሳ ፡ ዐብረውን ፡ የነበሩ ፡ ካህን ፥ ከሌሎች ፡ አሽከሮች ፡ ጋራ ፡ ኾነው ፥ ሕይወቱ ፡ ሳትወጣ ፡ ደርሰውለት ፥ ተረፈ ። ወዲያው ፡ የፖሊስ ፡ መርማሪዎች ፡ ጕዳዩን ፡ ሲመረምሩ ፡ ዐድረው ፥ በማግስቱ ፥ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ የሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ የፖሊስ ፡ አዛዥ ፡ የኾኑትን ፡ ብሪጋድዬር ፡ ጄኔራል ፡ ቀልቤሳ ፡ ቤካን ፦ *"ይህ ፡ ሰው ፡ ለምንድን ፡ ነው ፡ ራሱን ፡ ለማጥፋት ፡ የሞከረው ፧ ፈንጂውንስ ፡ በማን ፡ ላይ ፡ እና ፡ የት ፡ ሊያፈነዳው ፡ ነበር ፡ ያቀደው ፧ ማንስ ፡ ነው ፡ ይህን ፡ ተልእኮ ፡ የሰጠው ፧"* ብለው ፡ ጠየቋቸው ። ብ. ፡ ጄኔራል ፡ ቀልቤሳ ፡ ቤካ ፡ ሲመልሱ ፦ *"ክቡር ፡ ጄኔራል ፥ ሰውየውን ፡ ከሲዳሞ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አባረነዋል ፤ ሌላውን ፡ ነገር ፡ ለምን ፡ አይተዉትም ፧"* በማለት ፥ ከጸጥታ ፡ ጋራ ፡ ንክኪ ፡ ያለው ፡ ጕዳይ ፡ መኾኑን ፡ በመልሳቸው ፡ ጠቍመው ፥ የምርመራውን ፡ ውጤት ፡ ከመናገር ፡ ተቈጠቡ ።

ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፥ ከዚህ ፡ በፊት ፥ ኢትዮጵያን ፡ በልዩ ፡ ልዩ ፡ ኀላፊነቶች ፡ ሲያገለግሉ ፥ ከ 9 ፡ ያላነሱ ፡ ጊዜያት ፡ የግድያ ፡ ሙከራ ፡ ተፈጽሞባቸው ፥ በእግዚአብሔር ፡ ረድኤት ፡ ተርፈዋል ። ሲዳሞ ፡ ለጄኔራሉ ፡ የግድያቸው ፡ ምድር ፡ እንዲኾን ፡ በጨለማ ፡ ኀይሎች ፡ ተወስኖ ፥ ገና ፡ ከመድረሳቸው ፡ ይህ ፡ ውሳኔ ፡ በገዛ ፡ አሽከራቸው ፡ ሊፈጸምባቸው ፡ ነበር ። ርሱም ፡ ቢከሽፍ ፥ ሌሎች ፡ ኹለት ፡ የግድያ ፡ ሙከራዎች ፡ ተከታትለው ፡ ተቃጡባቸው ፤ እነርሱም ፡ በሚያስደንቁ ፡ ኹኔታዎች ፡ ከሸፉ ። ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ የእግዚአብሔር ፡ ጥበቃ ፡ እና ፡ ረድኤት ፡ አልተለይዋቸውም ፡ ነበርና ፥ ሲያመሰግኑት ፡ ኖሩ ።

ከመጨረሻው ፡ የግድያ ፡ ሙከራ ፡ በኋላ ፥ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ታክመው ፡ ከለንደን ፡ እንደተመለሱ ፥ ወዲያውኑ ፡ በምስከረም ፡ 1964 ፡ ዓ.ም. ፥ በመግሪብ ፡ (በ"ሞሮኮ") ፡ የኢትዮጵያ ፡ ባለሙሉ ፡ ሥልጣን ፡ እንደራሴ ፡ ተብለው ፡ ከኢትዮጵያ ፡ እንዲወጡ ፡ ተደረገ ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፥ ሲፈልጉ ፡ በሐሰት ፡ ክስ ፡ እና ፡ ደመ ፡ ወዝን ፡ በመከልከል ፡ (ከ 1933 ፡ ዓ.ም. ፡ እስከ ፡ 1963 ፡ ዓ.ም. ፡ ባሉት ፡ 30 ፡ ዓመታት ፥ ከሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ደመ ፡ ወዝ ፡ በድምሩ ፡ 77 ፡ ሺሕ ፡ ብር ፡ አላግባብ ፡ በመንግሥት ፡ ተይዞባቸው ፥ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ሳይመለስላቸው ፡ ቀርቷል) ፥ ሲብስባቸው ፡ ደግሞ ፡ በግድያ ፡ ሙከራ ፡ ሕይወታቸውን ፡ አስቸጋሪ ፡ አድርገውባቸው ፡ ነበርና ፥ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ የመግሪብ ፡ ሹመትን ፥ ምንም ፡ መዳረሻው ፡ እጅግ ፡ የራቀ ፡ ቢኾን ፥ እሮይ ፡ ብለው ፡ ተቀበሉት ።

መግሪብ ፡ ከገቡ ፡ ዓመት ፡ ሳይሞላ ፥ በ 1964 ፡ ዓ.ም. ፡ መጨረሻ ፡ ላይ ፥ 9 ኛው ፡ የአፍሪቃ ፡ አንድነት ፡ ድርጅት ፡ ጉባኤ ፡ እመግሪብ ፡ መዲና ፡ ሪባጥ ፡ ላይ ፡ ይካኼድ ፡ ነበርና ፥ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዐፄ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ በታላላቅ ፡ ባለሥልጣኖች ፡ ታጅበው ፡ ሪባጥ ፡ ገቡ ። ለተልእኮው ፡ ክብር ፡ በኢትዮጵያ ፡ መባሕታዊ ፡ ምንባር ፡ ትልቅ ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ተደረገ ። የልዕልት ፡ ተናኘ-ወርቅ ፡ ኀይለ-ሥላሴ ፡ ልጅ ፥ ኮሞዶር ፡ እስክንድር ፡ ደስታ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ዐጅበው ፡ መጥተው ፡ ነበር ። የዘውድ ፡ ምክር ፡ አባል ፡ እንደ ፡ መኾናቸው ፡ መጠን ፥ *"እገሌ ፡ ይሾም ፥ … ፡ እገሌ ፡ ይሻር ፥ … ፡ እገሌ ፡ ይከሰስ ፥ … ፡ እገሌ ፡ ይታሰር ፥ … ፡ እገሌ ፡ ይጋዝ ፥ … ፡ እገሌ ፡ ይገደል"* ብለው ፡ ዐብረው ፡ የሚመክሩም ፡ የሚወስኑም ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ አማካሪ ፡ ነበሩና ፥ ሊ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴን ፡ በእራት ፡ ግብዣው ፡ ላይ ፡ ሲያገኟቸው ፥ ከባዱን ፡


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ 2018 ፡ ዓ.ም. ።

ምስጢር ፡ እንደ ፡ ዋዛ ፡– *"ነጋ ! ብንልኽ ፡ ብንልኽ ፡ አልሞት ፡ ዐልከን ፡ እኮ ፡ "* ሲሉ ፡ ግልጥ ፡ አድርገው ፡ ነግረዋቸው ፤ የተፈጸመባቸውን ፡ በደል ፡ ኹሉ ፡ በዚህ ፡ ቃላቸው ፡ አረጋገጡላቸው ። ሌ. ፡ ጄኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ-ሥላሴም ፥ ይህን ፡ የድፍረት ፡ ንግግር ፡ በመገረም ፡ ታዝበው ፥ በልባቸው ፡– *"መጨረሻውን ፡ እስቲ ፡ እናያለን"* ፡ በማለት ፥ ጕዳዩን ፡ እንዳልሰማ ፡ ኾነው ፡ ዐለፉት ።

ኹለት ፡ ዓመት ፡ ሳይሞላ ፥ የየካቲት ፡ 1966 ፡ ዓ.ም. ፡ የመንግሥት ፡ ግልበጣ ፡ ዐመፅ ፡ ተነሥቶ ፥ ታሪክ ፡ የመዘገበው ፡ አስሠቃቂ ፡ ዕልቂት ፡ በኢትዮጵያ ፡ ምድር ፡ ተፈጸመ ።

ነገርን ፡ ነገር ፡ ያመጣዋልና ፥ ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፥ *"የሚያስተባብልብኝ ፡ አንድም ፡ ሰው ፡ የለ"* ፡ በሚል ፡ ትምክሕት ፡ ይመስላል ፥ እንደ ፡ ዋዛ ፡ የጐረጐሯቸው ፡ ጕዳዮች ፥ እንሆ ፥ ዘንዶን ፡ የሚያካክሉ ፡ ሌሎች ፡ ጕዳዮችን ፡ መዘው ፡ አወጡ ።

የግል ፡ ታሪክን ፡ እያበጃጁ ፡ የሌላን ፡ ማጠልሸት ፡ አልሰሜን ፡ ያስደምም ፡ እንደ ፡ ኾነ ፡ እንጂ ፥ የሰሙቱን ፡ እና ፡ የሚያውቁቱንስ ፡ በሆዳቸው ፡ ሲብላላ ፡ የኖረውን ፡ መራራ ፡ እውነት ፡ ሳይወዱ ፡ እንዲናገሩት ፡ ያስገድዳቸዋል ፡ እንጂ ፡ ዝም ፡ አያስሠኛቸውም ። *"ርጥቡ ፡ ሬሳ ፡ ደረቁን ፡ አስነሣ"* ፡ እንዲሉ ፥ እኔንም ፡ ይህን ፡ ማስታወሻ ፡ እንድጽፍ ፡ አስገደደኝ ።

በዛሬ ፡ ዘመን ፡ በኢትዮጵያ ፡ የምናየው ፡ በተለይ ፡ የታሪክ ፡ ቀባሪዎችን ፡ እንጂ ፥ የታሪክ ፡ ጸሓፊዎችን ፡ ለማየት ፡ ገና ፡ አልታደልንም ። ትኽክለኛ ፡ የታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡ የሚገነው ፡ ትኽክለኛ ፡ መንግሥት ፡ ሲቋቋም ፡ ብቻ ፡ ነውና ፥ ይህን ፡ ደኅኛ ፡ ፍጻሜ ፡ እስክናይ ፡ ድረስ ፥ በዘመናችን ፡ የታሪክ ፡ ጸሓፊዎች ፡ አለመኖር ፡ እያዘነ ፥ የታሪክ ፡ ተመራማሪዎች ፡ ባንኾንም ፡ እንኳ ፥ እንዲህ ፥ ታሪክ ፡ በቁሙ ፡ ሲቀበር ፡ እያየን ፡ ዝም ፡ ማለቱን ፡ ጠልተን ፥ ያቅማችንን ፡ ያኽል ፡ አበርክተናል ።

ደጃዝማች ፡ ወልደ-ሰማዕት ፡ ገብረ-ወልድ ፥ በሚያስመሰግናቸው ፡ ትጋት ፥ የግል ፡ ታሪካቸውን ፡ አሳምረው ፡ ለመጻፍ ፡ ሞክረዋል ። ከግላቸው ፡ እያለፉ ፡ ግን ፡ በዘለፋ ፡ መልክ ፡ የወረወሯቸው ፡ ቃላት ፣ የሸፋፈኗቸው ፡ ጕዳዮች ፣ የተሣለቁባቸው ፡ ቁም ፡ ነገሮች ፣ የተመጻደቁባቸው ፡ የግል ፡ ጥቅሞች ፥ ትርክታቸውን ፡ ለነፋስ ፡ ሰጥተውባቸው ፥ መጨረሻውን ፥ መጽሐፋቸው ፡ ጕድለቶቻቸውን ፡ ሳይከሥትባቸው ፣ ጥርጣሬዎችንም ፡ ሳያለማባቸው ፡ አልቀረም ❖


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2018 ፡ ዓ.ም. ።